# አግ 7 የአማራ መነሣሣት እንዲመታ ይፈልጋል ማለት ነው ወይ?

ይሄንን ለማለት ያስገደደኝ አግ 7 በኢሳትና በማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛዎች ባሰራጨው ዜና ወይም መረጃ መሠረት ሰሞኑን ጎንደር በተለያዩ ቦታዎች የወያኔ ግፍ አንገሽግሿቸው "ከፋኝ!" እያሉ እራሳቸውን አደራጅተው በጎበዝ አለቃ እየተመሩ በቆራጥነትና ድፍረት በተሞላበት ጀግንነት ግፈኛና አንባገነን አገዛዙን ለመደምሰስ ወያኔን እየተፋለሙ ካሉት የገበሬ ታጣቂዎች ጀርባ እንዳለና ያደራጃቸውም እሱ እንደሆነ በይፋ መግለጹ ነው፡፡

በመሆኑም ሁለት ነገሮችን ለማሰብ እንገደዳለን፡፡ አንደኛው ይሄንን ዜና የለቀቁ የአግ 7 ኃላፊዎች ፖለቲካን (እምነተ አሥተዳደርን) ካለማወቃቸው የተነሣ እንዲህ ብለው ማወጃቸው ወያኔን አስደንግጦ በእነዚህ አስፈላጊው የስንቅና ትጥቅ (የሎጅስቲክስ) አቅርቦት በበቂ ደረጃ በሌላቸው ይህች ሀገርና ሕዝባቸው ከቆሻሻው አንባገነን አገዛዝ ነጻ የማድረግ እልህና የጋለ ፍላጎት ብቻ የግድ ገፋፍቷቸውና ወያኔም አላስኖር ስላላቸው አሻፈረኝ እንዲሉ ተገደው የወጡ የገበሬ ታጣቂዎችን ወይም ተዋጊዎችን በአሸባሪነት በፈረጀው ግንቦት 7 ስም ፈርጇቸው ያለ የሌለ ኃይሉን በእነሱ ላይ በማፍሰስ እንዲያጠፋቸው መጋበዛቸው እንደሆነ ሳይረዱ ሳይገነዘቡ ወይም እወጃቸው የሚያስከትለውን አደጋና ጉዳት ሳያስተውሉ ለሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ ሲሉ ብቻ ይሄንን ዜና ለቀዋል የሚለው ሲሆን፡፡

ሌላው ደግሞ አግ 7 ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ከአማራ የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ማኅበራትና እኔን ከመሰሉ የአማራ አክቲቪስቶች (ስሉጣን) ጋራ በገባው ቅራኔ ምክንያት የአማራን መነሣሣት እንደ ሥጋት ቆጥሮ ይሄንን መነሣሣት በወያኔ አስጠቁሮ ለማስመታት ሲል ሆን ብሎ ይሄንን ዜና ለቋል የሚለው ነው፡፡

አግ 7 ይሄንን ስሕተት ሲሠራ ይሄ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ በባለፈው ሕዝባዊ የተቃውሞ፣ የእንቢተኝነት ወይም የዐመፅ እንቅስቃሴ ይደረግ በነበረበት ወቅትም ሕዝቡን ያነሣሣ የቀሰቀሰ እሱ እንደሆነ ተናግሮ ነበር ፡፡

አሁንም ያንኑ ስሕተት መልሶ ደገመው፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ ከተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች እውነቱ የትኛው እንደሆነ መለየት የምንችል አይመስለኝም፡፡ አንድ ነገር ግን ማለት የምንችል ይመስለኛል አግ 7 እንኳን ታጣቂዎቹ "ከፋኝ!" ብለው ለራሳቸው ስም በማውጣት በራሳቸው ተነሣሥተው እያደረጉት ያለውን ትግል እያደረጉ እንደሆነ እየገለጹ ቀርቶ አግ 7 እንዳለው ያደራጃቸው እሱ ራሱ ቢሆንም እንኳ የታጣቂዎችንና የሕዝቡን ደኅንነት አደጋ ላይ ላለመጣልና ለዘለቄታዊ ጥቅም ሲባል በፍጹም በፍጹም እንዲህ ብሎ ማወጅ አይገባውም ነበር፡፡ እናም እባካቹህ የአግ 7 ኃላፊዎች ሆይ! አስተውሉ! ብልህ ሁኑ! ከፍተኛ ጥንቃቄም አይለያቹህ! ኢሳትም እንደዛው!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com